**ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY**
**የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**
**ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE**
**የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/**

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 21/2011

ቀን፡ ጥቅምት 07 ቀን 2011 ዓ.ም

- ለ፡- ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ስ/ሂ
- ለ፡- ኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ስ/ሂ

- ከ፡- ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
  አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

አዝዘው ጫኔ አበበ
ስራ አስኪያጅ
Azizew Chanie Abebe
Manager

**ጉዳዩ፡- የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ የአሠራር ስርዓት መላክን ይመለከታል፣**

ከጉምሩክ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር በቁጥር 4.0/105/11 በቀን 05 ጥቅምት 2011 ዓ.ም በጻፈልን ደብዳቤ መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ላይ የሚስታወሉ የግልፀኝነት ችግሮች በተመለከተ በተለያየ ጊዜያቶች ከቅ/ጽ/ቤቶች ጥያቄዎች ሲነሱ የቆዩ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ችግሩን ለመቅረፍና ሲነሱ የነበሩ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ዕቃዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሲገቡ፣ ሲወጡ እና ሽያጭም ሆነ ምርት ሂደታቸውን ለማጠናቀቅ ከፓርኩ ወደ ሌላ ፓርክ ለመውሰድ ጥያቄዎች ሲቀርቡ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት ተልኮልናል።

በዚሁ መሠረት የተላከውን ማንዋል 17 ገጽ አያይዘን የላክንላችሁ በመሆኑ በተላከው ማንዋል መሠረት ተፈጻሚ እንዲሆን አሳውቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፡-
- ለ፡-ም/ሥራ አስኪያጅ /ሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ዘርፍ/
- ለ፡-ም/ሥራ አስኪያጅ /የጉምሩክ ጉዳዮች ዘርፍ/
- ለ፡-ህግ ማስከበር ም/ስራ አስኪያጅ
- ለ፡- ሕግ ማስከበር የስራ ሂደት
- ለ፡- ጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ
- ለ፡- ጉምሩክ /ሥ/ሥ/አ/የስራ ሂደት
- ለ፡- መጋዘን  አስተዳደር ቁጥጥር የሥራ ሂደት
- ለ፡- ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ሂደት
- ለ፡- ደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት

  አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No 2-0/2075/11
ቀን / Date 05 ጥቅምት 2011

ለኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን

ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ

አዲስ አበባ

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

ባሉበት

ጉዳዩ፡- የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ የአሠራር ሥርዓት መላክን ይመለከታል

በኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻፀም ላይ የሚስታወሉ የግልፀኝነት ችግሮች በተመለከተ በተለያየ ጊዜያቶች ከቅ/ጽ/ቤቶች ጥያቄዎች ሲነሱ ቆይቷል፡፡ በዚህ መሠረት ችግሩን ለመቅረፍና ሲነሱ የነበሩ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ዕቃዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሲገቡ፣ ሲወጡ እና ሽያጭም ሆነ ምርት ሂደታቸውን ለማጠናቀቅ ከፓርኩ ወደ ሌላ ፓርክ ለመውሰድ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ግልጽ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈልጓል፡፡

በዚሁ መሠረት ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ከዚህ ሸኝ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ በቀረበው 17 ገጽ የአሠራር ሥርዓት መሠረት እንዲፈፀም እያሳሰብን፤ በአሠራሩ ላይ የሚያጋጥሙ ክፍተቶች በአስቸኳይ ለጉምሩክ ዘርፍ እንድታሳውቁ እናስታውቃለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

ተስፋዬ ቱሉ መልካ
የጉምሩክ ዘርፍ ምክትል ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-
- ለክቡር ዋና ዳይሬክተር
- ለ ህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአምራቾችና ወጪ ንግድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን !!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የኢንድትሪ ፓርክ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት

ጥቅምት/2011

አድስ አበባ

Ethiopian Revenues and Customs Authority

1. መግቢያ

ሀገራት በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን እና ለሚያመርቷቸው ምርቶች ሰፊ ገበያ ለመፍጠር የተለያዩ የማበረታቻ ስርዓቶችን በመቅጽ ተግባራዊ ያደርጋሉ።

በሀገራችንም ቀደም ሲል ከተዘረጋው የኤክስፖርት የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ከተጠቀሱት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርክ/ዞን/ እንደ ሥርዓት የተቀመጠ ቢሆንም የአሠራር ሥርዓት ያልተቀመጠ በመሆኑናየሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የበለጠ ለማፋጠንና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር የተለያዩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በመገንባት ወደ ስራ እንዲገቡ እየተደረገ ይገኛል።

እነዚህ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለሀገራችን ከሚያስገኙት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ መካከል የስራ እድል ፈጠራ፣የቴክኖሎጂ ሽግግር፣የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ከመሆን ባሻገር የገቢ ዕቃን በሀገር ውስጥ ምርት መተካትንም ያጠቃልላል።

በመሆኑም የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት እና ልማትን ሊያፋጥኑ የሚችሉ አሰራሮችን ለመዘርጋት እና ለሀገር ውስጥም ይሁን ለውጭ ባለሀብት ሳቢ እና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007 ወጥቷል።

በተጨማሪም የተሻለ ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንዲኖር ብሎም የተቀናጀ እና የተሳለጠ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ለኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 417/2009 ወጥተዋል።

ባለሥልጣን መ/ቤቱም እነዚህን የሕግ ማእቀፎች እና የተለያዩ ሀገራት ልምድን መነሻ በማድረግ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሊያስፈጽማቸው የሚገቡ ተብለው በደንቡ እና በመመሪያ ውስጥ የተለዩ ዋና ዋና ተግባራትን በመለየት ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመቅርጽ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በዚህም መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ መስፈርቱን አሟልተው ወደ ስራ ለገቡ ባለሀብቶች የመብት ተጠቃሚነት ፈቃዳቸውን በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ ማዋላቸውን የሚያረጋግጥ የቁጥጥር እና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ሂደትን ያካተተ የአሰራር ሥርዓት ተዘጋጅቷል።

ይህ የአሰራር ሥርዓት በአዋጁ እና ደንቡ ላይ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ተግባራት የለየ እና ቀደም ሲል በተቀረጸው የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት ያልተካተቱትን በመለየት የአሰራር ስርዓቱን ትርጉም ቅድመ ሁኔታ እና ፈፃሚ አካላትን በሚያመለክት ዝርዝር መግለጫ የያዘ ነው።

2. የአሰራር ሥርዓቱ ዓላማ

   በኢንዱስትራ ፓርክ ውስጥ እና በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጪ ያሉ ድርጅቶች መካከል የምንከተላቸውን የሥራ ፍሰቶች ላይ ፈጻሚና አመራሩ ግልጽ በሆነ መልኩ ለመፈፀም እንዲያስችል የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት ነው።

3. ትርጉም

የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት ማለት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያሉ አምራቾች ጥሬ ዕቃ የሚያስገቡበት፣ ያለቀለትን ምርት ወደ ውጭ የሚልኩበት፣በከፊል ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚሸጡበት፣ከአንዱ የኢንዱስትራ ፓርክ ወደ ሌላው የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማስመረት ወይም በሽያጭ የሚያስተላልፉበት፣ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ሌላ አምራች የሚያስተላልፉበት ወይም የሚቀበሉበት፣ ተረፈ ምርት የሚወገድበት ሥርዓት ነው።

4. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚፈጸሙ ዋና ዋና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት
   1) ዕቃዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገቡበት ሥርዓት፣
   2) ዕቃዎች ከአንዱ የኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ሌላኛው የኢንዱስትሪ ፓርክ የሚተላለፉበት ሥርዓት፣
   3) ያለቀለት ምርት ወደ ውጭ የሚላክበት የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት፣
   4) ያለቀለትን ዕቃ ለግብዓትነት ሽያጭ የሚፈጸምበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የአሰራር ሥርዓት፣
   5) ያለቀለት ምርት በከፊል ሀገር ውስጥ ሲሸጥ የሚፈፀም የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት፣
   6) በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ላሉ አምራቾች እርስ በዕርስ ጥሬ ዕቃ ሲቀባበሉ የሚፈፀም የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት፣
   7) ተመርቶ ወደ ውጭ የተላከ ዕቃ በምክንያት ወደ ሀገር ውስጥ ተመልሶ የሚገባበት የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት ፣
   8) የተረፈ ምርት አወጋገድ የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት፣

9) ለኢንዱስትሪ ፓርክ ፣ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ ላለ ሌላ አምራች በሽያጭ (ምርት ለማጠናቀቅ) የሚያስተላልፉበት ወይም የሚቀበሉበት ሥርዓት

10)በኢንዱስትሪ ፓርክ የተመረቱ ምርቶች ናሙና ወደ ውጪ ስለሚላክበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

11)ከቀረጥና ታክስ ነጻ የገቡ ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም የተመረቱ ምርቶች የግብዓት ጥምርታ የሚወራረድበት የአሠራር ሥርዓት

በዚህ የአሰራር ሥርዓት ውስጥ በተራ ቁጥር 1፣ 3፣7 እና 11 ቀደም ሲል በተቀረጸው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት የሚስተናገድ ሲሆን ተራ ቁጥር 10 ላይ ያለው በናሙና አላላክ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚስተናገዱ ሲሆን ተራ ቁጥር 2፣4፣5፣6፣8 እና 9 የአሰራር ሥርዓት የስራ ሂደት የተቀረጸላቸው ናቸው፡፡

5. የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የስራ ሂደት

የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት ማለት ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኩ የሚገቡ ፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኩ የሚወጡ እና በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥና ወደ ሌሎች ማምረቻ እንዱስትዎች በሽያጭ ወይም በውል የሚተላለፉ ዕቃዎች የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት ነው፡፡

5.1. ዕቃዎች ከአንዱ የኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ሌላኛው የኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ላለ ሌላ አምራች ላኪ በሽያጭ የሚተላለፍበት የአሰራር ስርዓት

ሀ/ ትርጉም

ዕቃዎች ከአንዱ የኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ሌላኛው የኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ላለ ሌላ አምራች ላኪ በሽያጭ የሚተላለፍበት የአሰራር ሥርዓት ማለት ማንኛውም በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያለ አምራች ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ላለ ሌላ አምራች ላኪ ያመረተውን ምርት ወይም ጥሬ ዕቃ በመጠቀም ምርቱን ወደ ውጪ ለሚልክ ድርጅት በግብአትነት ሲያቀርብ የሚፈፀም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡


ለ/ የሰርጉቱ ተጠቃሚዎች

1) በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ተመዝግበው ፈቃድ ያገኙ አምራች ላኪዎች፣
2) በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ያሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፣
3) በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ያሉ ከፊል አመራቾች፣
4) ከኢንዱስትሪ ፓርክ ወጪ ያሉ አምራች ላኪዎች፣

ሐ/ ቅድመ ሁኔታዎች

1) ቀደም ሲል የገባበት ዲክላራሲዮን ኮፒ ለጥሬ ዕቃ፣
2) በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የፀደቀ የሽያጭ ውል ፣
3) ብሔራዊ ባንክ በሚዘረጋው አሠራር ሥርዓት መሠረት የሚሰጥ ፍቃድ፣
4) የተመዘገበ ወደ ፓርኩ ለሚመጣ የገቢ ድክራስዮን ፤ ከፓርኩ ለሚወጣ ደግሞ የገቢ ዲክለራሲዮን፣
5) የዉስጥ ትራንዚት ለማስፈቀድ የደብዳቤ ዋስትና ማቅረብ፣

መ/ የስራ ሂደት ሥዕላዊ በመግለጫ



ማስታወሻ፡- ይህ የስራ ፍሰት ከፓርኩ ውጪ ላሉ አምራቾች በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሠ/ የሥራ ሂደቱ ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ | | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| | | ከኢንዱስትሪ ፓርክ ለሚወጡ ዕቃዎች | ወደ ፓርክ ለሚገቡ ዕቃዎች | |
| 1 | የተሟሉ ሰነዶችን በመያዝ ጥያቄ ማቅረብ፣ | የመብቱ ተጠቃሚ | የመብቱ ተጠቃሚ | |
| 2 | የቀረቡት ሰነዶች የተሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | የጉምሩክ ሹም | የጉምሩክ ሹም | |
| 3 | ሰነዶቹ ተሟልተው ያልቀረቡ ከሆነ ወዲያውኑ እንዲያሟሉ ምላሽ መላሽ መስጠት፣ | የጉምሩክ ሹም | የጉምሩክ ሹም | |
| 4 | ዕቃውን በመፈተሽ በጉምሩክ ማሸጊያ ማሸግ | የጉምሩክ ሹም | | |
| 5 | የመንገድ ወረቀት በማዘጋጀት የውስጥ ትራንዚት መፍቀድ | የጉምሩክ ሹም | | |
| 6 | የመንገድ ወረቀት በመቀበል ዕቃው በተነሳበት ሁኔታ ስለመድረሱ ማረጋገጥ | | የጉምሩክ ሹም | |
| 7 | ቫሊዴት ማድረግ | | የጉምሩክ ሹም | |
| 8 | ቫልዴት መደረጉ በሲስተም ማረጋገጥ | የጉምሩክ ሹም | | |
| 9 | እስከ ዓመቱ መጨረሻ በተያዘው መረጃ መሠረት የገባ እና የወጣ ዕቃን የማስታረቅ ስራ ማከናወን እና ክሊራንስ መስጠት፣ | የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ኦፊሰር | የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ኦፊሰር | |

5.2. ዕቃዎች በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ወይም ከአንዱ የኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ሌላኛው የኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ባሉ አምራቾች የምርት ሂደታቸውን ለማጠናቀቅና ካጠናቀቁ በኋላ ወደ መጡበት የሚመለስበት የአሰራር ሥርዓት

ሀ/ ትርጉም

ይህ የአሰራር ሥርዓት ማለት ዕቃዎች ከአንዱ የኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ሌላኛው የኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ከኢንዱሰትሪ ፓርክ ውጪ ባሉ አምራቾች የምርት ሂደታቸውን ለማጠናቀቅና ካጠናቀቁ በኋላ ወደ መጡበት የሚመለሱበት የጉምሩክ የአሠራር ሥርዓት ነው፡፡

ለ/ የስርዓቱ ተጠቀሚዎች


1) በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያሉ አምራቾች፣
2) ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ያሉ አምራቾች፣

ሐ/ ቅድመ ሁኔታዎች

1. በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የፀደቀ ውል ወይም ደብዳቤ፣
2. ቀደም ሲል የገባበት ዲክላራሲዮን ኮፒ፣
3. የውስጥ ትራንዚት ዲ/ዮን፣
4. የደብዳቤ ዋስትና ማቅረብ፣
5. ዕቃው ተመርቶ ሲመለስ ለተሰጠው አገልግሎት ክፍያ የፈጸመበትን ደረሰኝ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 2
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

መ/ የስራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ




Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

ሠ/ የሥራ ሂደት ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ | | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| | | ከኢንዱስትሪ ፓርክ ለሚወጡ ዕቃዎች | ወደ ፓርክ/ሌላ ማምረቻ ቦታ ለሚገቡ ዕቃዎች | |
| 1 | የተሟሉ ሰነዶችን በመያዝ ጥያቄ ማቅረብ፣ | የመብቱ ተጠቃሚ | የመብቱ ተጠቃሚ | |
| 2 | የቀረቡት ሰነዶች በዕቃዉ አይነት እና ባህሪ የተሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | የጉምሩክ ሹም | የጉምሩክ ሹም | |
| 3 | ሰነዶቹ ተሟልተው ያልቀረቡ ከሆነ ወዲያውኑ እንዲያሟሉ ምላሽ መላሽ መስጠት፣ | የጉምሩክ ሹም | የጉምሩክ ሹም | |
| 4 | ዕቃውን በመፈተሽ በጉምሩክ ማሸጊያ ማሸግ | የጉምሩክ ሹም | | |
| 5 | የመንገድ ወረቀት በማዘጋጀት የውስጥ ትራንዚት መፍቀድ | የጉምሩክ ሹም | | |
| 6 | የመንገድ ወረቀት በመቀበል ዕቃው በተነሳበት ሁኔታ ስለመድረሱ ማረጋገጥ | | የጉምሩክ ሹም | |
| 7 | ቫሊዴት ማድረግ | | የጉምሩክ ሹም | |
| 8 | ቫልዴት መደረጉ በሲስተም ማረጋገጥ | የጉምሩክ ሹም | | |
| 9 | መረጃዎቹን በSoft copy እና በHard copy አደራጅቶ መያዝ፣ | የጉምሩክ መረጃ አደራጅ ኦፊሰር | የጉምሩክ መረጃ አደራጅ ኦፊሰር | |
| 10 | እስከ ዓመቱ መጨረሻ በተያዘው መረጃ መሠረት የገባ እና የወጣ ዕቃን የማስታረቅ ስራ ማከናወን እና ክሊራንስ መስጠት፣ | የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ኦፊሰር | የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ኦፊሰር | |

Ethiopian Revenues and Customs Authority ... Documentation No. 3

5.3. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚገኙ አምራች ድርጅቶች እርስ በራሳቸው የሚያከናውኑት ሽያጭ ላይ የሚፈፀም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

ሀ/ ትርጉም

በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚገኙ አምራች ድርጅቶች እርስ በራሳቸው የሚያከናውኑት ሽያጭ ላይ የሚፈፀም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ማለት በፓርኩ ውስጥ ፈቃድ ኖሯቸው በማምረት ተግባር ላይ የሚገኙ ድርጅቶች ያስገቡትን ጥሬ ዕቃ ተጠቅሞ ያመረቱትን ምርት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ለሚገኝ ለሌላ አምራች በግብዓትነት እንዲጠቀምበት በሽያጭ ሲያስተላልፉ የሚፈፀም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ነው።

ለ/ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች


1) በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ተመዝግበው በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች፣

ሐ/ ቅድመ ሁኔታዎች

1) በየ15 ቀን የተጠቃለለ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ጥሬ ዕቃው የገባበትን ቀዳሚ ዲክላራሲዮን ቁጥር ተጠቅሶ፣
2) የባንክ ፈቃድ ባንክ በራሱ በሚያወጣ አሰራር የሚፈጸም፣
3) የሽያጭ ውል ስምምነት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የፀደቀ፣
4) በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የግብዓት ምርት ጥምርታ፣

Revenue and Customs Authority ... No. 2

መ/ የስራ ሂደት ሥዕላዊ ማግለጫ




ሠ/ የስራ ሂደት ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሽያጭ የተፈጸመበት የተጠቃለለ ዲክላራሲዮንና ሌሎች ሰነዶች ማቅረብ፣ | የመብቱ ተጠቃሚ | |
| 2 | ሰነዶቹ እና ማስረጃዎቹ የቀረቡ መሆኑን አረጋግጦ ለቀጣይ ስራ ማስተላለፍ፣ | የጉምሩክ ሹም | |
| 3 | የቀረበውን ሰነድ ከቀዳሚ ዲክላራሲዮን በማመሳከር የሰነድ ምርመራ ስራ | የጉምሩክ ሹም | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ማከናወን፣ ተገቢውን የማጣራት ስራ በመስራት ሰነድ መበተን፣ | | |
| 4 | መረጃዎቹን አደራጅቶ በመያዝ ሰነዱን ወደ ዶክመንቴሽን ማስተላለፍ፣ | የመረጃ አደራጅ ኦፊሰር | |

### 5.4. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ተመርቶ ያለቀለትን ዕቃ በከፊል ሀገር ውስጥ ሲሸጥ የሚፈጸም የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት

ሀ/ ትርጉም

ያለቀለት ምርት በከፊል ሀገር ውስጥ ሲሸጥ የሚፈጸም የጉምሩክ አሰራር ስርዓት ማለት ማንኛውም በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚገኝ አምራች ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ያለ ቀረጥና ታክስ ያስገባውን ጥሬ ዕቃ ካመረተ በኋላ ምርቱን በከፊል አገር ውስጥ እንዲሸጥ የተስማማ ወይም በልዩ ሁኔታ በኢንቨስትመንት ቦርድ ተፈቅዶ ሲሸጥ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል የሚፈጸም የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት ነው።

ለ/ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች


1) በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ተመዝግበው ፈቃድ ያገኙ አምራች ላኪዎች፣
2) በኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኙ ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፣

ሐ/ ቅድመ ሁኔታዎች

1) ጥሬ ዕቃው የገባበት ቀዳሚ ዲክላራሲዮን፣
2) ሀገር ውስጥ እንዲሸጥ በሚመለከተው አካል የተሰጠ ፈቃድ፣
3) በኢንዱስትሪ ሚኒስተር የፀደቀ የግብዓት ምርት ጥምርታ
4) እንደ አስፈላጊነቱ የተቆጣጣሪና ተጓዳኝ መ/ቤቶች ፈቃድ፣
5) በጥሬ ዕቃው ላይ የተከፈለበት የቀረጥ እና ታክስ ዲክላራሲዮን

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

መ/ የስራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ




ሠ/ የስራ ሂደት ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ያለቀለትን ዕቃ በከፊል ለመሸጥ የተሟላ ሰነድ ለጉምሩክ ማቅረብ፣ | ባለመብቱ | |
| 2 | የቀረቡትን ሰነዶች ከቀዳሚ የጉምሩክ ሰነዶች ጋር ማመሳከርና ቀረጥና ታክስ ስሌቱ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ፣ | የጉምሩክ ሹም | |
| 3 | መረጃውን በአግባቡ መዝግቦ መያዝ እና ሰነዱ እንዲበተን ማድረግ፣ | የጉምሩክ ሹም | |
| 4 | የተበተነውን ዲክላራሲዮን በመያዝ ሽያጭ መፈፀም፣ | ባለመብቱ | |

5.5. በኢንዱስትሪ ፓርክ የተረፈ ምርት አወጋገድ ላይ የሚፈጸም የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት

ሀ/ ትርጉም

በኢንዱስትሪ ፓርክ የተረፈ ምርት አወጋገድ ላይ የሚፈጸም የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት ማለት ያለቀለትን ምርት ለማምረት በግብዓትነት የገባ ጥሬ ዕቃ በምርት ሂደት ውስጥ የሚገኝ ተረፈ ምርት በሽያጭ ወይም በሌላ አኳኋን የሚወገድበት የጉምሩክ የአሰራር ስርዓት ሂደት ነው፡፡


ለ/ የስርዓቱ ተጠቃሚዎች

1) በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙ አምራች ላኪዎች፣
2) በኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኙ ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፣

ሐ/ ቅድመ ሁኔታዎች

1) ተረፈ ምርቱ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሽያጭ ወይም በሌላ አኳኋን እንዲወገድ የተፈቀደበት ማረጋገጫ፣
2) የተረፈ ምርት መቶኛ መግለጫ ማስረጃ፣
3) የሚወገደው ተረፈ ምርት ታክስ ተከፍሎበት ከሆነ የተከፈለበት የሰነድ ማስረጃ፣
4) ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በሌላ አኳኋን የሚወገድ ከሆነ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲወገድ የተፈቀደበት ማስረጃ፣
5) እንደአስፈላጊነቱ የተጓዳኝ መ/ቤት ፈቃድ፣

መ/ የስራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ



ሠ/ የሥራ ሂደት ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ተረፈ ምርቱን ለማስወገድ ማመልከቻ እና አስፈላጊ ሰነዶችን አሟልቶ ማቅረብ፣ | ተጠቃሚው | |
| 2 | ሰነዶቹና ማስረጃዎቹ የተሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | የጉምሩክ ሹም | |
| 3 | ሰነዶቹ የተሟሉ ከሆኑ ተረፈ ምርቱ የሚወገድበት ሁኔታ በታክስ ወይም ያለታክስ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | የጉምሩክ ሹም | |
| 4 | ታክስ ተከፍሎበትየሚወገድ ከሆነ ታክሱ በአግባቡ የተከፈለ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲወገድ የሰነድ ማስረጃ መስጠት፣ | የጉምሩክ ሹም | |
| 5 | ያለታክስ የሚወገድ ከሆነ የቀረበውን ማስረጃ በማረጋገጥ ተረፈ ምርቱ እንዲወገድ በአካል መገኘት ወይም ማስረጃ መስጠት፣ | የጉምሩክ ሹም | |

Customs procedure codes

4052495:- Sales of goods for home use under export incentive schemes

5252496:- Sales of by-products under export incentive schemes

5252505:- sales of goods following temporary importation under voucher scheme to the same sector

5252506:-sales of goods following temporary importation under bonded manufacturing warehouse to the same sector

5252507:- sales of goods following temporary importation under bonded export manufacturing schemes to the same sector

5252508:-sales of goods following temporary importation under industrial park scheme to the same sector